# Amharic A: literature – Standard level – Paper 2
# Amharique A: littérature – Niveau moyen – Épreuve 2
# Amhárico A: literatura – Nivel medio – Prueba 2

Tuesday 1 May 2018 (morning)
Mardi 1 mai 2018 (matin)
Martes 1 de mayo de 2018 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

### Instructions to candidates

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the part 3 works you have studied and compare and contrast these works in response to the question. Answers which are not based on a discussion of at least two part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.
- The maximum mark for this examination paper is **[25 marks]**.

### Instructions destinées aux candidats

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. En basant votre réponse sur au moins deux des œuvres de la troisième partie que vous avez étudiées, vous devez comparer et opposer ces œuvres dans le cadre du sujet. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la troisième partie n’obtiendront pas une note élevée.
- Vous n’êtes pas autorisé(e) à apporter des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d’examen.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est de **[25 points]**.

### Instrucciones para los alumnos

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Conteste una sola pregunta de redacción. Base su respuesta en al menos dos de las obras estudiadas de la parte 3, comparándolas y contrastándolas en relación con la pregunta. Las respuestas que no se basen en al menos dos obras de la parte 3 no recibirán una puntuación alta.
- No está permitido traer copias de las obras estudiadas a la sala de examen.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[25 puntos]**.

2218 – 0012



© International Baccalaureate Organization 2018

ከሚከተሉት **አንዱን** ጥያቄ መልስ(ሽ):: መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) **ቢያንስ ሁለት** ስራዎች ላያ መመስረት አለበት:: ስራዎቹን **በማወዳደርና በማነጻፀር** ጥያቄውን መልስ(ሽ):: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላያ **ያልተመሰረተ** መልስ ከፍተኛ ነጥብ **አያስገኝም**::

## ድራማ/ተውኔት

1. ፀሐፌ ተውኔቶች እንዴትና ለምን አላማ አስቂኝ ገፀባህርያትን በስራዎቻቸው አቀረቡ? ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ድራማዎች በንፅፅር በማየት ጥያቄውን መልስ::

2. በድራማ በአብዛኛው ገፀባህሪያት ከተመልካቹ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በማድረግ "አራተኛውን ግድግዳ" ይሰብራሉ:: ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ተውኔቶች ይህ በምን መንገድ እንደቀረበ እና ውጤታማነቱንም አሳይ::

3. ጡዘት (ክላይማክስ) የተውኔት ዋነኛ ክፍል ነው:: ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ድራማዎች ውስጥ ጡዘት እንዴት እንደተፈጠረና ለምን አላማ እንደቀረበ በንፅፅር አስረዳ::

## ረጅም ልቦለድ

4. ስራዎቻቸውን ያጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ደራስያን ሃሳባቸውን ከሌሎች ገፀባህርያትና ከአንባቢው የደበቁ ማራኪ ገፀባህርያትን የፈጠሩባቸውን መንገዶችና ያስገኙዋቸውን ውጤቶች አስረዳ::

5. የገፀባህሪ አካላዊ አቋም በዝርዝር ሊቀርብም ሆነ ላይቀርብ ይችላል:: ባጠናሀቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች አካላዊ አቋም የቀረበበትን መንገድና ለስራው ያስገኘውን ጥቅም አሳይ::

6. የልቦለድ ደራስያን ሁነቶችን ሁልጊዜ በቅደም ተከተል አያቀርቡም:: ባጠናሀቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ደራስያኑ ያለቅደም ተከተል ታሪክ በማቅረባቸው ያገኙትን ውጤት በንፅፅር አስረዳ::

## ስነ ግጥም

7. ግጥም ቀላል ቃላትን ተጠቅሞ እንኳን ልብን የሚነካ ሊሆን ይችላል። ያጠናሀቸውን ሁለት ገጣምያን ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ የአረፍተ ነገሩን ትክክለኛነት አስረዳ።

8. ግጥም የእለት ተለት ሕይወትን በአዲስና ባልተለመደ መንገዶች ለማሳየት ይሞክራል። ያጠናቸውን ቢያንስ ሁለት ገጣምያን ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ይህ እንዴት ተግባራዊ እንደሆነ በንፅፅር አስረዳ።

9. ባጠናሃቸው ግጥሞች ውስጥ ቅሬታና ከሀዘን የመነጨ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት በእንዴት ያለ መንገድና በምን ያህል ውጤታማነት ቀረቡ? መልስህ የሁለት ገጣምያንን ስራዎች በንፅፅር የሚያሳይ ይሁን።

## አጭር ልቦለድ

10. አንዳንድ አጭር ልቦለዶች በግልጽ የተቀመጠ ሴራ (ፕሎት) ሲኖራቸው ሌሎቹ የላቸውም። ስራዎቻቸውን ያጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ደራስያን ሴራን እንዴትና ለምን አላማ እንደተጠቀሙበት በማወዳደርና በማነፃፀር አስረዳ።

11. ያጠናሀቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ምሳሌ በማድረግ ደራስያኑ የገፀባህርያታቸውን ሰብእና በውስጣቸው ባለው ግጭት አማካኝነት እንዴት እንዳቀረቡ አስረዳ።

12. በርካታ አጭር ልቦለዶች ድንገተኛ መግቢያ አላቸው። ስራዎቻቸውን ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ደራስያን አጭር ልቦለዶች በማነፃፀር ድንገተኛ መግቢያዎቹ ጥቅም ላይ በመዋላቸው በአንባብያን ላይ ያሳደሩትን ተጽእኖ አስረዳ።